መግቢያ

ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ዘገባ -- 1996/97
በዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብቶችና ሠራተኛ ጽ/ቤት ይፋ ተደረገ
የካቲት 21 ቀን 1997 ዓ.ም

ፕሬዚዳንት ቡሽ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ነፃነትን ማራመድና የሰውን ልጅ ክብር መጠበቅ የተሻለና የተረጋጋ ዓለምን ለመገንባት ያስችላል በሚል መርህ ላይ የተመሰረተ አዲስ የብሔራዊ ደህንነት ስልት ለዩናይትድ ስቴትስ እንዳዘጋጁ መስከረም 7 ቀን 1995 አቀረቡ፡፡ በሽብርተኝነት ላይ ከተከፈተው ጦርነት የተወለደውን ብሔራዊ ጥረት አቅጣጫ ለመስጠትና ለማሰባሰብ፤ ስልቱ ተከታታይነት ያላቸው መሰረታዊ ተግባራትን ደርድሯል፤ ከእነዚህም መካከል፣ መስተዳድራችን የሰብአዊ መብቶች ጥበቃንና የዲሞክራሲ ግንባታ ጥረቶችን እንዲደግፍ የሚጠይቁት ናቸው፡፡ ጥር 12 ቀን 1997 ሁለተኛውን የአገልገሎት ዘመናቸውን ለመጀመር ባሰሙት ንግግር፣ ፕሬዚዳንት ቡሽ ይህንን መርህ ይበልጥ አብራርተውታል፤ «የሀገራችን የነፃነት ሕልውና በሌሎች አገሮች ካለው የነፃነት መልካም ውጤት ጋር በጥብቅ የተያያዘ ነው፡፡ በአለማችን ሰላም እንዲሰፍን ያለው ተስፋ በዓለም ሁሉ ከነፃነት መስፋፋት ጋር የተያያዘ ነው፡፡» በ1996 ዩናይትድ ስቴትስና ዓለማቀፍ ተባባሪዎቿ ከብዙ አገሮች ጋር በመተባበር በሕብረተሰቦቻቸው ውስጥ የዜጎቻቸውን ፖለቲካዊ መብቶች በመንከባከብና የሕግ ልእልናን በማራመድ የነፃነትን አድማስ ለማስፋት ሲሰሩ ቆይተዋል፡፡ በጥቂት ሁኔታዎችም፣ በተለይም ትኩረቱ፣ ሕዝብ የራሱን መስተዳድር ለመምረጥ ያለውን መብት መጠቀሙ ዋና ጉዳይ በሆነባቸው ሥፍራዎች ላይ፤ ድራማዊ ክንውኖቹ የዓለምን ሕዝብ ቀልብ የሳቡና ታላላቅ ስኬቶችም ያስመዘገቡ ነበሩ፡፡

የታሊባን አገዛዝ በተወገደባቸው ባለፉት ሦስት ዓመታት ውስጥ የአፍጋኒስታን ሕዝብ ሽብርተኝነት እንዲቀንስና ደህንነቱ እንዲሻሻል ሲሰራ ቆይቷል፤ ነባር የዘር፣ የኃይማኖትና የጎሣ ክፍፍሎችን ለማጥበብ ጥረት አድርጓል፡፡ ከማህበራዊ አኗኗሩ የማይጋጭ፣ የሕዳጣንንና የሴቶችን መሠረታዊ መብቶች የሚያሰፋ፣ ሕብረተሰቡን ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ለፖለቲካዊ ውድድርና ሃሣብን በነፃነት ለመግለፅ የሚያስችል አዲስ ሕገ መንግሥት ቀርጿል፡፡ አለማቀፉ ሕብረተሰብ በበኩሉ ለዚህ የአፍጋኒስታን ሕዝብ ጥረት፤ እጅግ ሰፊ በሆነ መልካ ምድራዊ አቀማመጥ ተበታትነው የሚኖሩ እና በብዛኛው መሃይማን መራጮችን በመመዝገብ፣ የአፍጋሃኒስታን የምርጫ ሠራተኞችንና የፖለቲካ ተሳታፊ ካድሬዎችን ስለምርጫ አስተዳደርና ስለምርጫ ዘመቻ በማስተማር፣ እንዲሁም ከምርጫ በፊትና በምርጫው እለት ሂደቱ በሰላም እንዲፈፀም ከአፍጋሃን ኃይሎች ጋር በመተባበር በጎ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ በፕሬዚዴታዊው ምርጫም ተወዳዳሪዎቹ የአስር ሚሊዮን አፍጋሃኒስታዊያንን ድምፅ ለማግኘት ተፎካክረዋል፡፡ በዚህ፣ ጥቅምት 8 ቀን በተካሄደው ምርጫ፣ ከጠቅላላ መራጩ ሕዝብ 40% ሴቶች አፍጋሃኒስታዊያን ነበሩ፡፡ ብርቱ ማስፈራራትና አያሌ ቴክኒካዊ ችግሮች የነበሩበት የምርጫ ሂደት ቢሆንም 8 ሚሊዮን አፍጋሃኒስታዊያን -- ከእነዚህ መካከል 3.2 ሚሊዮኑ ሴቶች ነበሩ --- ወጥተው

ድምፃቸውን ሰጥተዋል፡፡ በዚህ ለመጀመሪያ ጊዜ በተከናወነ እውነተኛ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ አብዛኛዎቹ አፍጋሃኒስታዊያን ሃሚድ ካርዛይን ፕሬዚዳንታቸው አርገው መርጠዋቸዋል፡፡

በዩክሬይን በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ፣ በዘመቻው ወቅት መንግሥት በተቃዋሚ ተወዳዳሪዎች ላይ ያሳድር የነበረው አሉታዊ ተጽእኖ የምርጫ ዘመቻውን አበላሽቶት ነበር፡፡ በምርጫው እለትም ሰፊ የማጭበርበርና ሕገወጥ ተግባራት ተፈጽመዋል፡፡ የኩችማ መስተዳድር በመጀመሪያውና በሁለተኛው ምርጫ፤ ማለትም ጥቅምት 21 ቀን 1997 እና ሕዳር 12 ቀን 1997 በተካሄደው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ላይ የማጭበርበርና የማታለል ተግባራት ፈፀመ፡፡ መስተዳድሩ መገናኛ ብዙኃንን እና ጋዜጠኞችን ሳንሱር በማድረግ በዜና አዘጋገብ ላይ ተጽእኖ የማሳደር ተግባር ፈፀመ፤ ይኸ በተራው «የጋዜጠኛ አመፅ» እየተሰኘ የሚጠራውን እንቅስቃሴ የመስተዳድሩን መመሪያ አንቀበልም ባሉ ጋዜጠኞች አማካይነት ፈጠረ፡፡ በመጨረሻም ሕዳር 12 ቀን1997 በኦፊሴል ይፋ የተደረገውን የተጨበረበረ የምርጫ ውጤት አንቀበልም የሚሉ የሕዝብ ሰልፎች ቀስ በቀስ ወደ «ብርቱካናማው አብዮት» አደጉ፡፡ አብዮቱ ብርቱካናማ የተባለው፣ በምርጫው እንዳሸነፉ ይታመን የነበሩት የቪክቶር ዩሼንኮ የመወዳደሪያ ቀለም የብርቱካን ቀለም ስለሚመስል ነው፡፡

ሕዳር 24 ቀን 1997 የሀገሪቱ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በማጣሪያው ምርጫ ይፋ የተደረገውን ውጤት ሀሰተኛ እንደነበረ ሲበይን፣ በዩክሬን የሰብዓዊ መብቶች መከበር ወደ መልካምና ወሳኝ ወደሆነ አቅጣጫ ማምራቱ ታወቀ፡፡ የጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ውሳኔ፣ አያሌ የአገር ውስጥና ዓለማቀፍ የምርጫ ታዛቢዎች፣ ብዙ የምርጫ ሥርዓቶች እንደተጣሱ፣ የተቃዋሚ እጩዎች እንደተዋከቡ፣ በመንግሥት ቁጥጥር ስር በሚተዳደሩ መገናኛ ብዙኃን ስለሚፈፀመው ለአንድ ወገን ያደላ የዜና ሽፋን እና እጅግ ሰፊ የድምፅ አሰጣጥና ቆጠራ እንደተጭበረበረ የሰጡትን ቃል ሐቀኝነት ያረጋገጠ ነበር፡፡ ከፍርድ ቤት በተሰጠ ሥልጣን ታህሣሥ 17 ቀን 1997 በተካሄደው ምርጫ የዩክሬይን ሕዝብ አዲሱን ፕሬዚዳንቱን መረጠ፡፡

ዩሼንኮ ባሸነፉበት በዚህ ምርጫ ላይ ዓለማቀፍ ታዛቢዎች እንዳስተዋሉት ከሆነ፣ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን ተሻሽሏል፤ የምርጫው ሂደት ይበልጥ ግልፅ ሆኗል፤ የተለየ እጩ ድጋፍ እንዲያገኝ መስተዳድሩ ያደርግ የነበረው ተፅእኖ ቀንሷል፡፡ በምርጫው ወቅት የታዩ ችግሮችም ጥቂቶች ነበሩ፡፡ አዲሱ ፕሬዚዳንት ለዲሞክራሲ፣ ለሕግ ልእልናና ለሰብአዊ መብቶች ጥበቃ ያላቸውን ጥብቅ አቋም ገልፀዋል፡፡

በኢራቅ ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ መንገድ የራሱን መሪ ለመምረጥ በመዘጋጀት ላይ እያለ ብዙ ተደራራቢ አስቸጋሪ ተግባራትን ተጋፍጧል፡፡ የሽብርተኞች ጥቃት መጠናከርና በየስፍራው መበራከቱ ደግሞ የፈተናውን መጠን አስፍቶታል፡፡ በመጀመሪያ፣ የኢራቅ ገዥ ምክር ቤት በሕግ ልእልና ጥላ ስር እና በግልፅ በተደነገጉ ሥነ ሥርዓቶች የኢራቅ ዜጎች የራሳቸውን ባለሥልጣናት የሚመርጡበት፣ መንግሥታዊ ሥርዓታቸውን የሚገነቡበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሚያስችል የሽግግር ማእቀፍ ለማቆም ከሙሉ ስምምነት ደረሰ፡፡ በመጋቢት፣ የሽግግሩ አስተዳደር ሕግ ፀድቆ ለእነዚህ ግቦች መሳካት መንገድ ከፈተ፤ ሰኔ 21 ቀን 1996 ሉአላዊነቱ ከጊዜያዊ የቅንጅት ባለሥልጣን ወደ ኢራቅ ጊዜያዊ መንግሥት ተሻግሯል፡፡

ከተባበሩት መንግሥታትና ከሌሎች አለማቀፍ አማካሪዎች ጋር በመረዳዳት የኢራቅ ጊዜያዊ መንግሥት የኢራቅን ነፃ የምርጫ ኮሚሽን አቋቋመ፡፡ ይህ ኮሚሽን ኢራቅአዊያን፤ በ14 አገሮች ለሚኖሩ ኢራቅአዊያን ጨምሮ ለምርጫ የሚመዘገቡበትንና ድምፅ የሚሰጡበትን ሥነ ሥርዓትና ደንብ ቀረፀ፡፡ ከነሐሴ 9 እስከ 12 ቀን 1996 ድረስ የተሰበሰበው ብሔራዊ ጉባኤ 100 አባላት ያሉት ብሔራዊ ምክር ቤት አቋቋመ፡፡ የሀገሪቱ የሕግ አውጭ አካል የሆነውና ለኢራቅ የሽግግር መንግሥት ምሥረታ እንደ መጀመሪያ እርምጃ የሚቆጠረው የሽግግሩ ምክር ቤት አባላት ምርጫ ጥር 22 ቀን 1997 እንዲከናወን መርሃ ግብር ወጥቶ ነበር፡፡ በሽግግሩ አስተዳር ሕግ መሠረት፣ የሽግግሩ መንግሥት በመጪው ነሐሴ ወር 1997 የሚፀድቅ ቋሚ ሕገ መንግሥት ያረቅቃል፤ በፀደቀው ሕገ መንግሥት መሰረትም በታህሣሥ ወር 1998 ቋሚ መንግሥት ይመረጣል፡፡

ምርጫዎችን የመሰሉ ሕዝባዊ ክንውኖች (ኩነቶች) ሰላም እንዲሰፍን እድል ይሰጣሉ የሚል እምነት አለን፤ በእነዚህ አገሮች ውስጥ ራስን በራስ ለማስተዳደር ለሚደረገው ጥረት ጠንካራ መሠረት በመጣልና በእነዚህ እንቅስቃሴ ለሚካፈለው ሕዝብም ለሰብዓዊ መብቶች አጠባበቅ የሚደረገውን ትግል የሚያፋጥን ኃይል ለመፍጠር ያስችላል፡፡ 196 አገሮችን የሚያካትቱት እነዚህ ዘገባዎች በሚገባ እንደሚያመለክቱት ግን በዚህ አቅጣጫ የሚደረገው ጉዞ፣ ቢያንስ በመጀመሪያ ምዕራፎቹ ላይ ፈጣንና ቀላል አይሆንም፡፡ እነዚህ ዘገባዎች በግልፅ እንደሚያሳዩት በብዙ ቦታዎች፣ ለምሳሌ አምና በቬኔዙዌላ ዓለማቀፍ አካላት ሳይቀሩ የምርጫውን ፍትሃዊነትና ነፃነት የመሰከሩለት ዓይነት ምርጫ ከተፈፀመ በኋላ፣ የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ሲበላሽና መብቶች ሲሸረሸሩ ይታያል፡፡ በቬኔዙዌላ ከምርጫው በኋላ በፍትሕ አካሉና በመገናኛ ብዙኃን አኳያ የደረሰውም ይኼው ነው፡፡

በ1969 ኮንግሬስ ሀገራዊ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ መረጃዎች እንዲጠናቀሩና አመታዊ ዘገባ እንዲዘጋጅ፣ ይህንም ተግባር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስር ተቋማዊ ቅርጽ እንዲይዝ የወሰነው፣ በከፊልም ቢሆን የሰብአዊ መብቶችን አያያዝ ለማሻሻል የሚደረገው እንቅስቃሴ አስቸጋሪና ውስብስብ መሆኑን በመገንዘብ ነበር፡፡ ዓለማቀፉን የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ የሚመሰክረውን ይህን ዝርዝርና የተመጠነ ዘገባ ይፋ ስናደርግ፣ በአለማቀፉ የሰብአዊ መብቶች መግለጫ የተዘረዘሩትን የሰው ልጅ ክብር የተገለፀባቸውን ግቦች እውን ለማድረግ ይህ ዘገባ ለወደፊቶቹ ተግባራትና ትብብሮች ብርሃንና መሪ እንደሚሆን ተስፋ አድርገን ነው፡፡

ያለፈው ዓመት የዲሞክራሲ፣ የሰብአዊ መብቶችና የሠራተኛ ሁኔታ ሲመረመር በሚከተሉት ገጾች ከተመለከቱት የ196 አገሮች ዝርዝር ዘገባ በአንዳንድ አገሮች የተፈፀሙት ድርጊቶችና ተመክሮዎች ከሌሎች ጐልተው ይታያሉ፡፡ ይኼ የሆነው በነዚህ አገሮች ያለው የሰብዓዊ መብቶች አያያዝ ችግሮች መብዛት ብቻ ሳይሆን በ1996/97 ዓ.ም እኛም ከመስተዳድሮቹና ከሰለባዎቹም ጋር በነበረን ግንኙነትም ጭምር ነው፡፡

የሱዳን መስተዳድር የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ታሪኩ እጅግ በጣም ደካማ ነው፤ የንግግርን፣ የፕሬስን፣ የመሰብሰብን፣ በማህበር የመደራጀትን፣ የኃይማኖትን ነፃነት ሸብቧል፡፡ መብቶቻቸውን የተጠቀሙትንም አዋክቧል፤ አስሯል፡፡

በአመቱ መጨረሻ ላይ ከ1.5 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በዳርፉር ግዛት ውስጥ ተፈናቃይ ሆኗል፤ ሌሎች 200,000 የሚሆኑ ሰላማዊ ሰዎች ደግሞ ወደ ቻድ ተሰድደዋል፤ የስደተኞቹን መከራ ለማቃለል የማቀናጀቱን ሥራ ያከናወነው የመንግሥታቱ ድርጅት የስደተኞች ጉዳይ ከፍተኛ ኮሚሽነር ነው፡፡ ወደ 70,000 የሚገመቱ ሰዎች በዚህ በኃይል የማፈናቀል ተግባርና በደረሰው ጥቃት እንደሞቱ ተዘግቧል፡፡

መስተዳድሩ ከኃይል እርምጃ ለመታቀብ በተደጋጋሚ ቃል ቢገባም፣ በዳርፉር ውስጥ አሁንም ጥቃቱ እንደቀጠለ ነው፡፡ መስተዳድሩና በመስተዳድሩ የሚደገፉ ጀንጃዊድ የሚባሉ የሚሊሺያ ኃይሎች በመደበኛ ተግባርነት በዳርፉር ሰላማዊ ዜጎች መንደሮች ላይ ጥቃት ፈፅመዋል፡፡ ጃንጃዊዶች፣ አብዛኛውን ጊዜ ከመደበኛ የመንግሥት ኃይሎች ጋር በመተባበር ወታደራዊ የአየር ከለላ እየተሰጣቸው ጥቃት ፈፅመዋል፡፡ ባለፈው መስከረም ወር፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ኮሊን ፖዌል ኤክስፐርቶች በ1,100 ስደተኞች ላይ ያካሄዱትን ጥናት በጥንቃቄ ከመረመሩ በኋላ በዳርፉር ሕዝብ ላይ የዘር ማጥፋት ወንጀል እንደተፈፀመበት ከድምዳሜ ደርሰዋል፡፡ «በዳርፉር ውስጥ የዘር ማጥፋት ወንጀል ተፈፅሟል፤ ለዚህም ተጠያቂዎቹ የሱዳን መንግሥትና ጃንጃዊዶች ናቸው፤ ዛሬም ቢሆን የዘር ማጥፋት ወንጀሉ እየተፈፀመ ሊሆን ይችላል፡፡» በማለት ነበር የደረሱበትን መደምደሚያ ይፋ ያደረጉት፡፡

የመንግሥት ኃይሎች በዚያ ክልል ለጥቃት ተግባር በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ ሁሉ ገድለዋል፣ አቁስለዋል፣ ሰላማዊ ሰዎችን ከመኖሪያቸው አፈናቅለዋል፣ ክሊኒኮችንና የሰዎችን መኖሪያ ሆን ብለው አውድመዋል፡፡ በመንግሥት የሚደገፉ ሚሊሺያዎችም ሆን ብለው ሰላማዊ ሰዎችን ማጥቃታቸው፣ ንብረታቸውን መዘረፋቸው እና መንደሮቻቸውን ማውደማቸውን ያረጋገጡ ዘገባዎች አሉ፡፡

በተመሳሳይ ጊዜም፤ በአመቱ መጨረሻ ላይ፣ በሰሜንና ደቡብ ሱዳን ዙሪያ የተከሰተውን ግጭት ለመፍታት በተደረገው ድርድር የተገኘው ውጤት በሌሎችም የሱዳን ግዛቶች ለሰላምና ለሰብአዊ መብቶች አያያዝ መሻሻል ተስፋ ፈንጥቋል፡፡ በአመቱ መጨረሻ ላይ ለ21 ዓመታት ሲካሄድ ከቆየው ግጭት በኋላ በመንግሥትና በሱዳን ሕዝብ ነፃነት ሠራዊት መካከል የመጀመሪያ ደረጃ ስምምነት ለመፈፀም የሚደረገውን እንቅስቃሴ፣ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመልክቷል፡፡

የሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኮሪያ (ሰሜን ኮሪያ) መንግሥት በሕዝቡ ላይ ለሚያደርገው ያልተቋረጠ ጨካኝ የእመቃ አገዛዝ ምላሽ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት የ1996ን የሰሜን ኮሪያ የሰብአዊ መብቶች ሕግ አጽድቋል፡፡ ሕጉ በሰሜን ኮሪያ የሚገኘውን የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፤ ለሰሜን ኮሪያ ስደኞች ዘላቂና ሁነኛ መፍትሔ እንዲገኝ፣ ሰብአዊ እርዳታ የሚሰጥባቸው ዘዴዎች ግልፅ እንዲሆኑ፣ ነፃ የመረጃ ፍስሰት እንዲኖር እና በኮሪያ ባህረ ገብ መሬት ላይ ሰላማዊ ውህደት እንዲፈፀም ትኩረት ይሰጣል፡፡

በቤላሩስ፣ ፖሊስ ሥልጣኑን አላግባብ መጠቀሙን እንደቀጠለ ነው፤ አልፎ አልፎም በቁጥጥር ስር ባሉ ሰዎችና በእስረኞች ላይ የስቃይ ተግባር ይፈጸምባቸዋል፡፡ የደህንነት ኃይሎቹ በማን አለብኝነት ፖለቲካን እንደምክንያት አድርገው ዜጎችን አግተዋል፣ አስረዋል፤ ከዚህ ሌላም፣ አንዳንድ ግለሰቦች የመንግሥት ባለሥልጣናትን «ስም አጥፍታችኋል» የሚል ክስ ቀርቦባቸው ተፈርዶባቸው ታስረዋል፡፡ «ስም ማጥፋት» የተሰኘው ወንጀል በብዙ ሁኔታ በፖሊሲ ላይ የቀረበ ሂስንም እንዲጨምር ሆኖ የተበየነ ነው፡፡ ለረዥም ጊዜ አድራሻው ያልታወቀውን ጋዜጠኛና የታወቁ ተቃዋሚ ፖለቲካ መሪዎችን በኃይል በመሰወር ረገድ የመንግሥት እጅ እንዳለበት የተረጋገጡ ዘገባዎች ቢቀርቡም፣ የቤላሩስ መንግሥት ዘገባዎቹን በማጣጣል፣ እነዚህን ድርጊቶች ግልጽ በሆነና በተሟላ መንገድ ለማጣራት በአሻፈረኝነቱ ፀንቷል፡፡ ይባስ ብሎም፣ መንግሥት በእነዚህ ወንጀሎች ውስጥ እጃቸው እንዳለበት ተጨባጭ ማስረጃ በአውሮፓ መማክርት ዘገባ ላይ የቀረበባቸውን ቪክቶር ሼይማንን የፕሬዚዳንቱ አስተዳደር ኃላፊ አድርጎ በመሾም የባለሥልጣናትን ከሕግ በላይ የመሆን አዝማሚያ እንዲጠናከር በማድረጉ ቀጥሎበታል፡፡

በበርማ፣ ወታደራዊው መንግሥት ያለ አንዳች ሕገ መንግሥታዊ ድንጋጌ በአዋጅ ትእዛዞች ብቻ ሲገዛ ቆይቷል፡፡ የደህንነት ኃይሎች ሕገወጥ ግድያ ፈፅመዋል፡፡ በተጨማሪም የዜጎች በኃይል መሰወር ቀጥሏል፤ የፀጥታ ኃይሎች በጥበቃ ሥር ያሉትንና እስረኞችን አስገድደው ደፍረዋል፣ አሰቃይተዋል፣ ደብድበዋል፣ ወይም የተለያዩ በደሎች አድርሰውባቸዋል፡፡ ያለ በቂ ምክንያት መታሰርና ከዘመድ ወዳጅ እንዳይገናኙ ከልክሎ በእስር ማሰቃየት የሚደጋገሙ ድርጊቶች ነበሩ፡፡ የደህንነት ኃይሎች መደበኛ በሆነ መልኩ የዜጎችን ግላዊ መብት ደፍረዋል፤ የአንድ አካባቢ ሕዝብን በግድ ወደ ሌላ አዛውረዋል፤ ሕፃናትን ለውትድርና መልምለዋል፡፡

የኢራን መንግሥት ከሕጋዊነት ውጭ በተፈረዱ ቅጣቶች የገደላቸውን ዜጎች ጨምሮ ባለፈው ዓመት ለአያሌ ግድያዎች ተጠያቂ ነው፡፡ የደህንነት ኃይሎች እስረኞችንና በጥበቃ ሥር ያሉትን ሰዎች ማሰቃየታቸውን የሚያስረዱ አያሌ ዘገባዎች ነበሩ፡፡ በተጨማሪም አለምክንያት እስራቶች ተፈፅመዋል፤ ከጠያቂ አግልሎ ለረዥም ጊዜ ማሰር፣ የተጨናነቁና የተፋፈጉ እስር ቤቶች፣ የሕግ አማካሪ እጦት፣ የግርፊያ ቅጣት፣ ግላዊ መብትን መጣስ የመሳሰሉት የተፈፀሙ ግፎች ናቸው፡፡

በ1996/97 ዓ.ም ሰብአዊ መብቶችን በተመለከተ የቻይና መንግሥት ያደረገው ትብብርና እርምጃ ተስፋ የሚያስቆርጥና የሚያሳዝን ነበር፡፡ ቻይና በ1994 በዩናይትድ ስቴትስና በቻይና መካከል ተካሂዶ በነበረው የሰብአዊ መብቶች ውይይት ላይ ለመፈፀም ቃል ገብታባቸው የነበሩ ጉዳዮችን ሳትፈፅም ቀርታለች፡፡ ይሁንና በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን ስብሰባ ላይ ዩናይትድ ስቴትስ በቻይና የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ላይ ቀርቦ የነበረውን ውሳኔ በመደገፏ ተቋርጦ የነበረው የሁለቱ አገሮች የባለሙያዎች ውይይት ባለፈው ዓመት መጨረሻ ላይ እንደገና ቀጥሏል፡፡ በ1996 ዓ.ም የቻይና መንግሥት ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ የሚያደርጉ ዜጎችን ማሰሩንና በጥበቃ ስር ማቆየቱን (ማገቱን) ቀጥሎበታል፡፡ በኢንተርኔት

በነፃነት የሚወያዩ፣ የተቃዋሚዎችንና የደሆችን መብት በሕግ ለማስጠበቅ ሲሉ በተከላካይነት የሚሟገቱ ጠበቆች፣ የኤች አይ ቪ/ኤድስን ጉዳይ አንስተው የሚሟገቱት፣ ሳርስ በተባለው ተዛማች በሽታ ላይ የዘገቡ ጋዜጠኞች፣ የፖለቲካ አስተሳሰባቸውን በይፋ የሚናገሩ ምሁራን፣ የቤት ውስጥ አምልኮን የሚከታተሉ ክርስትያኖችና ለመብታቸው የተከራከሩ ሠራተኞች የእዚህ ዓይነቱ እስር ሰለባዎች ምሳሌዎች ናቸው፡፡ በቻይና ወህኒ ቤቶች ውስጥ ሕገወጥ ድርጊቶች ቀጥለዋል፡፡ ፋሉንጎግ በተባለው መንፈሳዊ ንቅናቄ ላይ የቻይና መንግሥት የሚያካሂደውን አፈና አልተቋረጠም፡፡ በአስር ሺህዎች የሚቆጠሩ የንቅናቄው ተሳታፊዎች ዛሬም ቢሆን በእስር እየማቀቁ ይገኛሉ፤ በሥራ ካምፖች እና በአእምሮ ሕክምና ማእከላት አማካይነት ሕገወጥ ትምህርት ይሰጣቸዋል፡፡ የሀገሪቱ ሕዝባዊ ሸንጎ በሕገ መንግሥቱ የሰብዓዊ መብቶችን አጠባበቅ የሚደነግጉ አንቀጾች እንዲታከሉ ማሻሻያ አድርጎ የነበረ ቢሆንም፤ መንግሥት እነዚህን ማሻሻያዎች እስከምን ድረስ ለመቀበል እንዳቀደ ግልጽ አይደለም፡፡

በሳዑዲ አረቢያ፣ በጥቂት ዘርፎች አዎንታዊ እድገቶች ነበሩ፤ በመንግሥት ድጋፍ የተካሄደው በሴቶች መብትና ግዴታ ላይ የተካሄደው ጉባኤና በንጉሱ ግዛት ፈቃድ ያገኘው የመጀመሪያው መደበኛ የሰብአዊ መብቶች ድርጅት ከአዎንታዊ እድገቶች መካከል የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ ባለፈው ጥቅምት ወር መንግሥቱ ለአያሌ አመታት በሀገሪቱ ሰኖሩ ባእዳን ለዜግነት መብት እንዲያመለክቱ ደንብ ማውጣቱ፣ በአመቱ መጨረሻ ደግሞ ሴቶችን ያገለለ ቢሆንም፣ የካቲት 1997 ዓ.ም ለሚካሄደው የመዘጋጃ ቤቶች ምርጫ የመራጮችና የእጩዎች ምዘገባ ማካሄዱም፣ ሌሎች የሚጠቀሱ መልካም እርምጃዎች ናቸው፡፡

በሳዑዲ አረቢያ የሚፈፀመው የሰብአዊ መብቶች ጥሰትና ረገጣ ዘገባ ግን ተደረጉ ከተባሉት አወንታዊ እርምጃዎች በእጅጉ የሚበልጥ ነው፡፡ የደህንነት ኃይሎች በእስረኞች ላይ የሚፈፅሙት ሰቆቃና ሕገወጥ ተግባራት፣ ከምክንያት ውጭ እስራት እና አግልሎ በጥበቃ ስር ማዋልን የመሳሰሉ ድርጊቶች መፈፀማቸውን የሚያረጋግጡ ዘገባዎች አሉ፡፡ ኃይማኖታዊ የፖሊስ አባላት፣ ዜጎችንም ሆነ ባእዳንን ማንገራበድና ማገት እንደቀጠሉ ናቸው፡፡ አብዛኞቹ ችሎቶች ዝግ ናቸው፤ ስለሆነም ተከሳሾች ብዙ ጊዜ ችሎት የሚቀርቡት የሕግ ምክር ሳያገኙ ነው፡፡ ለለውጥ የቆሙትንም የደህንነት ኃይሎች አስረዋቸዋል፤ አግተዋቸዋል፡፡ መንግሥቱ ዛሬም ቢሆን የመናገርንና የፕሬስን፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀትና ከቦታ ወደቦታ የመዘዋወርን ነፃነት እንደከለከለ ይገኛል፡፡ በግል ነፃነት ላይም መንግሥት የሚፈፅመው ጥሰት ተዘግቧል፡፡ በሴቶች ላይ የሚፈፀም አድሎና ጥቃት፣ በሕፃናት ላይ የሚደርሰው ጥቃት፣ በኃይማኖትና በሌሎች ሕዳጣን ማሕበረሰቦች የሚደርሰው መድሎ እና በሠራተኞች መብት ላይ የጣለው ብርቱ እቀባ ዛሬም እንደቀጠለ ነው፡፡

በብዙ አገሮች እያደገ ከሚገኘው፣ ዜጎች በመንግሥት ባለሥልጣናት ላይ ካላቸው ቀጥተኛ ቁጥጥር በተቃራኒ፣ በሩሲያ የፓርላማ ምርጫን ለመወሰን የወጡት ሕጎችና የክፍለ ሀገር ገዥዎችን በሕዝብ ድምፅ በቀጥታ ከመምረጥ ይልቅ በሹመት መደረጉ፣ የሕግ አስፈጻሚውን አካል ጉልበት ይበልጥ አጠናክሮታል፡፡ በመገናኛ ብዙኃን ላይ የቁጥጥር ዘዴዎች መጠናከራቸው፣ ታዛዥ ፓርላማ፣ በቅርብ ጊዜ በተካሄደው ምርጫ የታዩ ጉድለቶች፣ ሕጋዊ

ውሳኔዎች ተግባራዊ ሲደረጉ ያለው ሙስናና በፍትሕ ሥርዓቱ ላይ የሚደርሰው ፖለቲካዊ ተጽእኖ፣ የመንግሥትን ተጠያቂነት እየሸረሸረው ነው የሚለውን ስጋት ከፍ አድርጎታል። ሕጋዊ ክልከላዎች ያሉ ቢሆንም ዘርን መሠረት ያደረገ ጥቃትና መድልዎ ጨምሯል። በሕዳጣን ላይ የሚፈፀምባቸውን በደል ባለሥልጣናቱ አይመረምሩትም፤ በተቃራኒው ግን የሕዳጣኑን የመኖሪያ ሰነዶች ለመፈተሽ አይቦዝኑም፤ ይህም የሚደረገው ከከተሞች አካባቢ ለማስወጣት፣ ከሚችሉት በላይ የገንዘብ ቅጣት ለመጣልና በተደጋጋሚ ለእስር እንዲዳረጉ ለማመቻቸት ነው። የመንግሥት ተቋማት ሰብአዊ መብቶችን ለመጠበቅ ያላቸው ፍላጎት በአንፃራዊ ሁኔታ ሲታይ በጣም ዝቅተኛ ነው።

የዚምባቡዌ መንግሥት የተቀናጀ የጥቃት፣ የእመቃና የማንገራበድ ዘመቻ አካሂዷል። ለሰብአዊ መብት አጠባበቅ፣ ለሕግ ልእልናና ለዚምባቡዌ ዜጎች ደንታ ቢስነት ማሳየት የዘመቻው መለያዎች ናቸው። የፖለቲካ ተቃዋሚዎችና የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች በተለያዩ ዘዴዎች ሰቆቃ ይፈፀምባቸዋል። የቀድሞ የዚምባቡዌ ተዋጊዎች፣ የወጣት ብርጌዶች (ቡድኖች) እና የፖሊስ ኃይሎች በፖለቲካ ጠላቶች ላይ የማያባራ የጭካኔ ተግባር ይፈፅማሉ። የሙጋቤ መንግሥት፣ ፖሊስንና የፍትሕ አካላቱን ጨምሮ ሌሎች የመንግሥት ተቋማትንም የጥቃቱ ኢላማ አድርጓቸዋል። ዳኞችን አስፈራርቶ ማንበርከብ ወይም ሥራቸውን በገዛ ፈቃዳቸው እንዲለቁ በማድረግ ሥፍራቸው በሙጋቤ ደጋፊዎች ይሞላል። የዜና ማሰራጫ ዘዴዎች ተሸብበዋል፤ ታፍነዋል፤ አጠፉ የሚባሉ ጋዜጠኞችም ይታሰራሉ፣ ይደበደባሉ። የመሬት ቅሚያው፣ የፖለቲካና ማኅበራዊ ጭቆና መሣሪያ ሆኖ እንደቀጠለ ነው። ይህንን የሚቃወሙ ኃይሎችም የብርቱ ጥቃት ሰለባዎች ሆነዋል።

ባለፈው ነሐሴ ወር በተደረገው ውሳኔ ሕዝብ የፕሬዚዳንት ቻቬዝ መንግሥት ከሥልጣን ለመቆየት ቢችልም፣ በ1996/97 ዓ.ም በቬኔዙዌላ የታየው የሰብአዊ መብት አያያዝ ደካማ ነበር።

የውሳኔ ሕዝቡን ሂደት ተቃዋሚዎች ማጭበርበር የተመላ ነው ቢሉም፣ በአሜሪካ መንግሥታት ድርጅትና በካርተር ማእከል ታዛቢዎች ይፋ የተደረገው ውጤት «የመራጩን ሕዝብ ፍላጐት ያንፀባርቃል» ብሏል። መንግሥት በሕግ ተርጓሚው ክፍል ላይ የሚያደርገውን ቁጥጥርና በፍትሕ ሥራዎች ላይ የሚፈፅመውን ጣልቃ ገብነት አመቱን በሙሉ ቀጥሎበታል። መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችንም ከመንግሥት ደጋፊዎች ማስፈራራትና ማንገራበድ ደርሶባቸዋል። ባለፈው ታህሣሥ ወር የሕግ አውጭው አካል የመገናኛ ብዙኃንንና የንግግር ነፃነትን የሚሸረሽር ሕግ አውጥቷል። ድንጋጌዎቹ በመንግሥት ላይ የሚሰነዘርን ነቀፋ ወይም ሂስ እንደ ወንጀል ድርጊት የሚቆጥሩ ናቸው። የቬኔዙዌላ መንግሥት የሰዎችን ንግድ ለመዋጋት በቂ ጥረት ባለማድረጉ የዩናይትድ ስቴትስ መንግሥት ማእቀብ ጥሎበታል።

ፊደል ካስትሮ፣ በዓለም ለረዥም ዓመት በሥልጣን የቆየ አምባገነን በመሆን ያላቸውን ሬከርድ (ክብረ ወሰን)፣ አምና አንድ ዓመት አክለውበታል። መንግሥቱ ምንም ዓይነት ዲሞክራሲያዊ ለውጥ ላለመቀበል ይዞት የቆየውን አቋም ቀጥሎበታል። የዲሞክራሲ ደጋፊዎችን፣ ተቃዋሚዎችን፣ ጋዜጠኞችንና ከመንግሥት ቁጥጥር ውጭ የሆኑ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን ለመጀመር የሚፈልጉ ባለሙያዎችንና ሠራተኞችን ማስፈራራቱንና ማዋከቡን

አላቆመም፡፡ ዓለማቀፍ ተቃውሞ ቢኖርም፣ በ1995 ረዥም የእስራት ቅጣት ከተወሰነባቸው 75 ተቃዋሚዎች መካከል አብዛኞቹ ዛሬም በእስር ቤት እየተሰቃዩ ናቸው፡፡ ባለሥልጣናቱ ይባስ ብለውም ተጨማሪ 22 የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችን «ባለሥልጣንን በማዋረድ» በሚልና በመሳሰሉ ክሶች ወንጅለው እስራት ፈርደውባቸዋል፡፡ ዩናይትድ ስቴትስ፣ እንደ ተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ኮሚሽን አባልነቷ፣ በኪዩባ የሚፈፀመውን የሰብአዊ መብቶች ረገጣ ትኩረት መስጠቷን ትቀጥልበታለች፡፡

ኮሚሽኑ በ1996 በነበረው ጉባኤ፣ በኪዩባ ላይ፣ በዩናይትድ ስቴትስ የተደገፈውን ውሳኔ ተቀብሏል፤ በተጨማሪም፣ በቱርክሜኒስታን፣ በሰሜን ኮሪያና በቤላሩስ በተከታታይ ለሁለተኛ ጊዜ ውሳኔውን በመደበኛ አሰራሩ አጽድቆታል፡፡ በበርማ ላይ የተላለፈው ውሳኔም በሙሉ ድምፅ ነበር፡፡ የራሳቸውን ዜጎች መብቶች የማያከብሩና የማይንከባከቡ እንደ ዚምባቡዌ፣ ኪዩባ፣ ሱዳን እና ቻይና ያሉ አገሮች አባል የሆኑበት የኮሚሽኑ የ1996 ጉባኤ በብዙ ረገድ ያልተሳካ ነበረ፡፡ ኮሚሽኑ በቻይና፣ በዚምባቡዌና በቼቺኒያ ስለሚፈፀሙት የሰብአዊ መብቶች ጥሰት የቀረቡትን የውሳኔ ሃሣቦች አልተቀበላቸውም፡፡ የኮሚሽኑን አሠራር ማሻሻል እንደሚያስፈልግ ዩናይትድ ስቴትስ ማሳሰቧን ቀጥላለች፤ በተለይም የተሻለ የሰብአዊ መብቶች አያያዝ ታሪክ ያላቸው አገሮች የኮሚሽኑ አባል እንዲሆኑ ታሳስባለች፡፡

በዲሞክራሲያዊ መንገድ ሥልጣን የያዙ መንግሥታት የዜጎቻቸውን ሰብአዊ መብት በማክበር ረገድ የተሻለ እንደሚሆኑ ዩናይትድ ስቴትስ ታምናለች፡፡ በዚህም ምክንያት፣ ዩናይትድ ስቴትስ የዲሞክራሲዎች ማሕበር በሚል ስያሜ ሕብረት ከፈጠሩ አገሮች ጋር ተባብራለች፡፡ ይህ ማህበር ወይም መረብ፣ ዲሞክራሲን በመላው ዓለም እንዲስፋፋ፣ እንዲጠናከርና ሥር እንዲሰድ ዲሞክራሲያዊ አገሮች አብረው የሚሰሩበት ነው፡፡ በ1996 ዩናይትድ ስቴትስ ከዴሞክራሲዎች ማህበር አገሮች ጋር በመተባበር አንድ የዲሞክራሲ ቡድን ተመስርቷል፡፡ ይህ ቡድን ተመሳሳይ አቋም ያላቸውን አገሮች የያዘ ሲሆን በኮሚሽኑና በሌሎች የመንግሥታቱ ማሕበር አካላት ውስጥ ከዲሞክራሲያዊ እሴቶች ጋር የሚስማሙ ግቦችን ለማቀናጀት ያስችላል፡፡ በተባበሩት መንግሥታት የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ ኮሚሽን ውስጥ ዩናይትድ ስቴትስ ከፔሩ፣ ሮማኒያ እና ምሥራቅ ቲሞር ጋር በመሆን የመንግሥታቱ ድርጅት ዲሞክራሲን በማስፋፋት ረገድ ያለውን ድርሻ ከፍ የሚያደርግ ውሳኔ እንዲተላለፍ በማድረግ በኩል ተሳክቶላቸዋል፡፡ የፀደቀው ውሳኔ ከሚያቀርባቸው ሃሣቦች መካከል አንዱ፣ በኮሚሽኑ ጽ/ቤት ውስጥ ዴሞክራሲን ለመገንባት ለሚሞክሩ አዳዲስ ዴሞክራሲዎች ከመንግሥታቱ ድርጅት ሀብት ድጋፍ የሚያጋኙበትን ስልት የሚቀይስ አካል እንዲቋቋም የሚጠይቅ ነው፡፡

የዲሞክራሲዎች ማህበር በተመድ ውስጥ ከፍ ብሎ የተጠቀሰውን ቡድን (ኮከስ) ከመፍጠሩ ባሻገር፣ ዲሞክራሲያዊ ተቋማት እና እሴቶች የሚጠናከሩበትን መንገድ በመፈለግ በተለያዩ ፕሮጀክቶች ዲሞክራሲያዊ ሀገሮች ትስስር እንዲፈጥሩ አድርገዋል፡፡ በዚህም ሕብረ ብሔራዊ ልዑካንን ወደ ምሥራቅ ቲሞር ልኮ ዲሞክራሲያዊ ተመክሮአቸውን ለቲሞራዊያን ባለሥልጣናት አካፍለዋል፡፡ በተመሳሳይም፣ ከምርጫ ጋር ግንኙነት ያላቸው የኢራቅ ባለሥልጣናት ከኢራቅ ወደ ሊትዌኒያ በመጓዝ ስለምርጫ ሂደት ተመልክተዋል፤ ተምረዋል፡፡ መሠረታዊ የሆኑትን

የሰብአዊ መብቶች፣ ማለትም በዓለማቀፍ የሰብአዊ መብቶችም መግለጫ የተካተቱትንና በዋርሶ በተካሄደው የደሞክራሲዎች ማህበር መግለጫ፣ እንዲሁም በሴኡል የተግባር እቅድ ላይ የተካተቱት እነዚህ መብቶች እንዲከበሩ የተባበረ ድምፅ ማሰማቱ የገዛ ዜጎቻቸውን መብቶች በሚነፍጉ መንግሥታት ላይ የሚደረገውን ተጽእኖ ቀጣይነት ያረጋግጣል፡፡

ተቋማዊ ለውጦች

በካታር በኤሚሩ ፈቃድ የተጀመረው አዲስ ሕገ መንግሥት የማርቀቁ ሂደት እንደቀጠለ ነው፡፡ አዲሱ ረቂቅ ሕገ መንግሥት በ1995 በመራጩ ሕዝብ አብዛኛ ቁጥር ተደግፏል፡፡ የኤሚሩ ቤተሰብ የዘር ተዋረድ ስልጣኑን የማይለቅ ቢሆንም፤ በ1997 ሰኔ ላይ ተግባራዊ እንደሚሆን የሚጠበቀው አዲሱ ሕገ መንግሥት አያሌ ሰብአዊ መብቶችን የሚያስጠብቁ ድንጋጌዎች ይዟል፡፡

በፓኪስታን ባለፈው ዓመት መጨረሻ ላይ ወታደራዊ ሥልጣናቸውን ለመልቀቅ አስታውቀው የነበረ ቢሆንም፣ ፕሬዚዳንት ሙሻረፍ አሁንም በዚያው ወታደራዊ ስልጣናቸው ላይ እንዳሉ ናቸው፡፡

በአፍሪካ ውስጥ፣ የማእከላዊ አፍሪካ ሬፐብሊክ መጋቢት 1995 ዓ.ም በመፈንቅለ መንግሥት ሥልጣን በያዙት ፕሬዚዳንት ቦዚዜ አማካይነት አዲስ ሕገ መንግሥት በሥራ ላይ አውላለች፤ ወደ ዲሞክራሲ ለሚደረገው ሽግግርም ተጨማሪ እርምጃዎችን ወስዳለች፡፡ በጊኒ ቢሳዎ በመስከረም 1993 (94) ላይ ወታደራዊ መፈንቅለ መንግሥት ከተደረገ በኋላ ወታደሩ የሲቪል መንግሥት አቋቁሟል፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች፣ ከመፈንቅለ መንግሥቱ በኋላ በታየው መረጋጋት ይዘገቡ የነበሩ የሰብአዊ መብቶች ጥሰት ቁጥር ቀንሷል፡፡

ወደ አውሮፓ ሕብረት ለመቀላቀል የሕብረቱን የኮፐንሄገን መስፈርት ለማሟላት ቱርክ ያሳየችው ፍላጎት፣ የተለያዩ ለውጦችን ለማካሄድ መንግሥቱን ገፍቶታል፡፡ ከነዚህም ለውጦች መካከል አዲስና በአንፃራዊ ሁኔታ ሲታይ ለዘብተኛ የወንጀል ሕግ፣ የፍልሚያ ግድያዎችንና ሰቆቃን የሚከለክሉ፣ የሃይማኖትን፣ ሃሣብን የመግለፅ፣ የመደራጀት ነፃነትንና ወታደራዊ ኃይሉ በመንግሥት ሥራ ያለውን ድርሻ የሚገድቡ ድንጋጌዎች በሕገ መንግሥቱ ተካትተዋል፡፡ ይሁንና የእነዚህ ድንጋጌዎች ተግባራዊነት ተጓትቷል፡፡ የደህንነት ኃይሎች፣ ሰቆቃ መፈጸምን፣ ድብደባን፣ ሕገወጥ እስራትንና ይዞ ማቆየትን ጨምሮ አያሌ ሕገወጥ ተግባራትን መፈፀማቸውን አልተዉም፡፡ ይሁንና ታዛቢዎች እነዚህ ድርጊቶች እንደቀነሱ ይናገራሉ፤ የአውሮፓ የሰቆቃ መከላከያ ኮሚቴም፣ የአካባቢ ባለሥልጣናት፣ ማዕከላዊ መንግሥት ምንም ዓይነት የሰቆቃ ተግባር እንዳይፈፀም ያወጣውን ደንብ ለመተግበር ብርቱ ጥረት እንደሚያደርጉ ዘግቧል፡፡ የፍልሚያ ግድያዎች ቀጥለዋል፡፡ መንግሥት በአንዳንድ ቋንቋዎችና በኩርድ ቋንቋ አጠቃቀም ላይ የጣለውን ገደብ ቢያላላም፣ በንግግርና በፕሬስ ነፃነት ላይ የጣለው ገደብ እንዳለ ነው፡፡

ያለፈው ዓመት የተለያዩ መንግሥታት ሙስናን ለመዋጋት፣ ከፍ ያለ ጥረት ያደረጉበት ነበር፡፡ የቀድሞ ከፍተኛ ባለሥልጣናትን በመመርመር ረገድ ጥብቅ እርምጃ የወሰደችው አገር ኮስታሪካ ናት፡፡ ቀደም ሲል በሥልጣን ላይ የነበሩት ሦስት ፕሬዚዳንቶች የሙስና ጉዳይ

ማለትም፣ ሕገወጥ የገንዘብ አጠቃቀም፣ የውስታ መመላለስንና ሕገወጥ ኮንትራቶችን በተመለከተ ልዩ ምርመራ ማካሄድ ጀምራለች፡፡ በአፍሪካ ውስጥም፣ ፀረ ሙስና ዘመቻው የማይገባቸውን ገንዘብ በሚያጋብሱና በሰብአዊ መብት ረገጣ በሚጠረጠሩ ባለሥልጣናት ላይ አትኩሯል፡፡ የጋምቢያው ፕሬዚዳንት ጃሜህ ዘመቻ ማእከል ያደረገው፣ አለማቀፍ ታማኝነትን ለማትረፍ ሲባል የባለሥልጣናትን የሙስና ተግባር በመቆጣጠር ላይ ነው፡፡ የተቋቋመው አጣሪ ኮሚሽን ሥራም ከፍተኛ ባለሥልጣናትን እስከማባረርና በኢኮኖሚ ወንጀል የተጠረጠሩትን ለፍርድ እስከማቅረብ ደርሷል፡፡ ኬኒያም ፀረ ሙስና ተቋም መስርታ፣ መንግሥት በሕገወጥ ግድያዎች የተጠረጠሩትን ሰዎች ጉዳይ እያጣራ ይገኛል፡፡ በዛምቢያ በፖሊስ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የሚያጣራ ተቋም በ1995 ላይ ተመስርቶ የቀረቡ ቅሬታዎችን በመመርመር ላይ ይገኛል፡፡

የፖለቲካ መብቶች

ከጆርጂያና ከዩክሬይን በስተቀር በዩሬዢያ የሚታየው የፖለቲካ እድገት በጣም አሳሳቢ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ያለው እድገት የሚለካው በሲቪል ሕብረተሰቡ እድገት አኳያ ነው፡፡ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቁጥራቸው እያደገ የሚሄድ መያዶች (መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች)፣ ተቃዋሚ ፓርቲዎችና ዜጎች፣ ለመደራጀትና የመንግሥት ተጠያቂነት እንዲኖር እየታገሉ ናቸው፡፡ በቱርክሜኒስታንና በኡዝቤኪስታን ተቃዋሚ ፓርቲዎች ሕጋዊ እውቅና ተሰጥቶአቸው ሊመዘገቡ አልቻሉም፡፡ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ የአካባቢው መንግሥታት ከዩክሬይንና ከጆርጂያ ክፉ ክፉውን ምሳሌ በመቅሰም የሲቪል ማህበሮችን በማፈንና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ደግሞ ቢሮክራሲያዊ በሆነ ስልት እያዋከቧቸው ይገኛሉ፡፡

በ1996 ጥር ላይ በጆርጂያ በተደረገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በዓለማቀፍ ታዛቢዎች የተስተዋለው መሻሻል፣ መጋቢት ላይ ለተከናወነው የፓርላማ አባላት ምርጫ መልካም መድረክ በማዘጋጀቱ «በጆርጂያ ታሪክ እጅግ ዲሞክራሲያዊ ምርጫ» የተባለለትን ምርጫ ለማከናወን ተችሏል፡፡ በዚሁ አካባቢ የሚገኙ ሌሎች መንግሥታትም የምርጫ ሕጎችን በማሻሻል የተወሰኑ እርምጃዎች ወደፊት ተራምደዋል፡፡ በካዛኪስታን፣ በኪርጊስታንና በታጂኪስታን የወጡት አዳዲስ ሕግጋት የመሻሻል ምልክቶች ሊሆኑ ይችላሉ፤ ይሁንና በሦስቱም አገሮች የወጡት ሕግጋት ከአለማቀፍ ደረጃ አኳያ ሲታዩ ብዙ የሚጐድላቸው ናቸው፡፡ ስለሆነም በ1996 በካዛክስታንና በኪርጊስታን የተካሄዱት ምርጫዎች ከቀደሙት ምርጫዎች የተሻሉባቸው ብዙ አልነበረም፡፡ የአገር ውስጥና የውጭ ታዛቢዎች እንደሚሉትም በምርጫዎቹ ወቅት የድምፅ መዛባት፣ የተቃዋሚ እጩዎችን ማዋከብ ወይም በነሱ ላይ ሕገወጥ ድርጊት መፈፀም፣ ወይም በመገናኛ ብዙኃን እኩል እድል አለማግኘት በሰፊው የታዩ ጉድለቶች ናቸው፡፡

በቤላሩስ መንግሥት ሕዝቡ በዲሞክራሲያዊ መንገድ በገዛ ነፃ ፈቃዱ የራሱን መንግሥት ለማቋቋም ያለውን ሕጋዊ መብት መንፈጉን እንደቀጠለበት ነው፡፡ ባለፈው ጥቅምት 6 ቀን በተካሄደው የተጭበረበረ ውሳኔ ሕዝብ በሕገ መንግሥት ተደንግጐ የነበረው የፕሬዚዳንቱ የሥራ ዘመን ገደብ እንዲነሳ ተደርጓል፡፡ ይህ ውሳኔ ሕዝብና በተመሳሳይ ሁኔታ ማጭበርበር